# Refugee agencies help and advice

June 2008 Amharic

# ከ 5 መጋቢት 2007 ዓ.ም በፊት ለጥገኝነት ያለመለከቱና እንግሊዝ አገር ለመኖር ፍቃድ ያልተሰጥዎት ነዎትን?

መልስዎ 'አዎን' ከሆነ፡ ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ በአገር ውስጥ ጉዳይ ጽህፈት ቤት የእንግሊዝ አገር የድንበር ኤጀንሲ (UK Border Agency - UKBA) አካል የሆነው በጉዳይ አፈጻጸም ዲረክቶረት (Case Resolution Directorate) ጽሕፈት ቤት ጉዳዩ እስካሁን እየታየ መሆኑን ያሳያል። ይህ ዲረክቶረት እስካሁን ውሳኔ ላለተሰጣቸው የጥገኝነት ማመልከቻዎችን ይመለከታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ 2011 ዓ.ም፡ አብዛኞቹ ከመጋቢት 2007 ዓ.ም በፊት የቀረቡትን ጥያቄዎች ይመረምራል።

በተጨማሪም ዲረክተሩ ለጥገኝነት ጠያቂዎች ጉዳያቸው እንዴት እየተመረመረ መሆኑን ለማሳወቅ ደብዳቤ እየላከ ይገኛል።

## ከእንግሊዝ አገር የድንበር ኤጀንሲ (UKBA) ደብዳቤ ከተቀበሉ በኃላ ምን ለማድረግ ይገባዎታል?

አብዛኛው ጊዜ ከ UKBA የሚላከውን ደብዳቤ ቀጥሎ ያሉትን ይዞታዎችን ያካተተ ይሆናል፤

- ጉዳይዎን ለምርመራ እንደተመረጠ የሚገልጽ ማብራርያ
- የጉዳይዎ ሃላፊ  አድራሻ የሚገልጽ
- የሕግ እርዳታ እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ
- ሰዎች ወደ ትውልድ አገራቸው በፍላጎታቸው እንዴት ለመመለስ እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ

በተጨማሪም UKBA ጽሕፈት ቤት ለሕግ ወኪልዎ (ካልዎት) የደብዳቤውን ግልባጭ መላክ አለበት።

የ UKBA ጽሕፈት ቤት የጉዳይዎችን ዝርዝር መረጃዎች በመላክ፡ የተገለጹትን መረጃዎች ትክክል መሆናቸውንና አለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሊጠይቅዎት ይችላል። በተጨማሪም እርስዎ ወይም የህግ ወኪልዎ በ **21** ቀኖች ውስጥ ወደ UKBA ጽሕፈት ቤት የጉዳይዎ ሃላፊ መላክ የሚገባቸውን ተጨውማሪ መረጃዎችን እንዲልኩ ደብዳቤው ሊጠይቅዎት ይችላል። ስለሆነም የሚላከውን መልእክት ይህን ደብዳቤ ከተቀበሉ በኃላ በ **21** ቀኖች ውስጥ ወደ የ UKBA ጽህፈት ቤት መድረሱን ማረጋገጥ የእርስዎ ወይም የሕግ ወኪልዎ ሃላፊነት ይሆናል።

ይህን ደብዳቤ ከተቀበሉ ወዲህ ተጨማሪ ምክርና እርዳታ መፈለግ የበለጠ ሃሳብ ነው – ቀጥሎ ያለውን ገጽ ይመልከቱ። ምንም እንኳን የሕግ አማካሪ ባያገኙ ለደብዳቤው በግዝየው መልስዎን መስጠት አለብዎት፡ ነገርግን የሕግ ምክር እንደሚፈልጉ በመልስዎ ላይ ማሳወቅ አለብዎት። ወደ UKBA ጽህፈት ቤት የሚልኳቸውን ማንኛውም ወረቀት ለራስዎ ቅጂ መያዝና ወደ የ UKBA ጽሕፈት ቤት ለሚያደርጓቸው የስልክ ደወሎችን በሙሉ ማስታውሻ መያዝ ይገባል።

## የጉዳይዎ ሃላፊ ሥም የማያውቁት ከሆነ እንዴት ከUKBA  ጋር ለመገናኘት ይችላሉ?

ከ UKBA የሚላከውን ደብዳቤ ሳይላክሎት ሁኔታዎን እንደተቀየረ (ለምሳሌ፡ ልጅ ከወለዱ፡ ካገቡ ወይም አድራሻ ከቀየሩ) ለ UKBA ጽህፈት ቤት ለማሳወቅ ከፈለጉ፡ ወደ የኢምግሬሽን ጥያቄ ቢሮ (Immigration Enquiry Bureau - IEB) በስልክ ቁጥር 0870 606 7766 ደውለው ማነጋገር ይችላሉ።



Asylum Support Partnership is a partnership project hosted by the British Refugee Council
British Refugee Council, (commonly called the Refugee Council) is a company limited by guarantee registered in England and Wales, [No 2727514] and a registered charity, [No 1014576].
Registered office: 240-250 Ferndale Road, London SW9 8BB, United Kingdom

የ IEB ጽሕፈት ቤት የመለያ ቁጥር፣ ሥም፣ የትውልድ ቀን እና ለጥገኝነት ያመለክቱበትን ቀን ይጠይቃል። ከዛ በኃላ የ IEB ጽህፈት ቤት ስለተቀየረው ሁኔታ ለጉዳይዎ ሃላፊ እንዲያሳውቁት አድራሻ ይሰጥዎታል። የ IEB ጽህፈት ቤት ጉዳይዎን መቼ እንደሚወሰን ሊነግርዎት አይችሉም። የሚኖሩበት አድራሻ ከቀየሩ አዲሱ አድራሻዎን ወደ IEB ጽሕፈት ቤት ስልክ በመደወል ለማሳወቅ ይችላሉ።

## የ UKBA ጽህፈት ቤት አሁን ጉዳየን እንዲያየው ለማድረግ ይቻላል ወይ?

ልዩ በሆነ ምክንያት ጉዳይዎን አሁን መታየት አለበት የሚል ስሜት ካልዎት የህግ ወኪልዎን ለማነጋገር ይችላሉ። የ UKBA ጽህፈት ቤት በህግ ወኪልዎ ወይም በፓርላመንት አባልዎ (MP) የተጻፉት የጽሁፍ ውክልናዎችን ለመቀበል ተስማምተዋል።

## የ UKBA ጽህፈት ቤት ለሁሉም ጥገኝነት ጠያቂዎችን ደብዳቤ እየጻፈ ነውን?

አይደለም። የ UKBA ጽህፈት ቤት ለአንዳንድ ጉዳያቸውን የሚመረምርላቸው የጥገኝነት ጠያቂዎች ደብዳቤ አይልክም። ለምሳሌ፣ ባለጉዳዩ ወንጀል ከፈጸመ፣ የ UKBA ሕግን ካላከበረ፣ ወይም በህገወጥ ስራ ሲሰራ ከተገኘ፣ የእንግሊዝ አገር የድንበር ኤጀንሲ ከአገሩ እስኪያወጣው ድረስ ደብዳቤው የመቀበል ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው። ስለጉዳይዎ የሚጨነቁ ከሆነ የሕግ ምክርን ይፈልጉ - ከዚህ በታች ይመልከቱ።

እላይ ከተጠቀሱት ሰዎች መካካል ባለመሆንዎ የሚተማመኑ ከሆኑና የ UKBA ጽህፈት ቤት የእርስዎን የአሁኑ ጊዜ መረጃ ያለው ከሆነ ደብዳቤ እንዲላክልዎት በትእግስት ቢጠብቁ ይመረጣል። ሆኖም ግን፣ ከ UKBA ጽህፈት ቤት የሚላከውን ደብዳቤ ከተቀበሉ በቂ ጊዜ (21 ቀኖች) ስሌልዎት የሚያስፈግዎትን ምክር ተሎ ብለው ማግኘት አለብዎት።

የ UKBA ጽህፈት ቤት ጉዳይዎን በተመለከተ ሊያውቀው የሚፈልጉት ነገር ካለ፣ አስቀድመው የህግ ምክር ማግኘት አስፈላጊ ነው።

## ምክርን ማግኘት

*ማድረግ ያለብዎት ነገር፣*

- *አስቀድመው ጉዳይዎን የሚከታተል የሕግ ወኪልን ማነጋገር ወይም*
- *ሊረዳዎት የሚችል የሕግ ወኪል ፈልገው ማግኘትና ደብዳቤው ከተቀበሉ በኃላ ሊረዳዎት እንደሚችል አስቀድመው ማረጋገጥ ይገባል።*

**የማህበረሰብ የህግ አገልግሎት (Community Legal Advice)** ጽሕፈት ቤት በስልክ ቁጥር 0845 345 4345 ደውለው የሕግ ወኪል ሊያገኙና የትኛው የሕግ ወኪል ወይም ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎት የሚችል ማህበር ጋ መሄድ እንዳለብዎት ሊነግርዎት ይችላሉ። ሌላው አማራጭ ደግሞ ይህን ድረገፅ መጎብኘት ይችላሉ። www.communitylegaladvice.org.uk

የሚያነጋግሩት የሕግ ወኪል የሚሰራበት ማህበር በኢምግሬሽን ሕግ ከየህግ አገልግሎት ኮሚሽን (Legal Services Commission) ጋር ኮንትራክት ያለው ወይም ከ **የኢምግረሽን አገልግሎት ኮሚሽነር (Office of the Immigration Services Commissioner - OISC)** ጽህፈት ቤት ጋር የተመዘገበ አማካሪ መሆን አለበት። ስለ ጥገኝነት ሕግን በተመለከተ ምክር ለማቅረብ ፍቃድ ያላቸው ማህበሮች ዝርዝር ስም ከፈለጉ የ OISC ጽህፈት ቤትን በስልክ ቁጥር 0845 000 0046 ደውለው ለመጠየቅ ወይም በድረገጻቸው www.oisc.gov.uk መመልከት ይችላሉ።

የሕግ ወኪልዎ ለሕግ እርዳታ ለማግኘት ማመልከት ስለሚችል ለሚሰጥዎትን አገልግሎቶች ወጪ መክፈል የለብዎትም። የረፍዩጂ ኤጀንሲ አባል ሰራተኛ፣ የሕግ ወኪል የት ማግኘት እንደሚችሉ ሊነርግዎት ይችላል።

የሕግ ወኪልዎን በሚያነጋግሩበት ጊዜ ቀጥሎ ያሉት ነገሮችን ማተዋል ይገባል፣

- አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች በሙሉ ለምሳሌ የዋናው የጥገኝነት ወረቀት ቅጂ፣ እንደተከለከሉ የሚገጹ ደብዳቤዎች፣ ከጥገኝነትና ኢምግሬሽን ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችና ከዛ ወዲህ የነበረውን ማንኛውንም አይነት ግኑኝነት የሚያሳዩ ሰነዶችን እንደያዙ ማረጋገጥ ይገባል።

- የነዚህ ሰነዶች ቅጂ በሙሉ መያዝና በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበት ቦታ ማስቀመጡ ጥሩ ሃሳብ ነው። ለምሳሌ በ UKBA ጽህፈት ቤት ከታሰሩ፡ ማንኛውንም ዘመድዎ ወይም ጓደኛዎ ሰነዶችን በቀላሉ አግኝቶ ሊያመጣልዎት ይችላል።

## ከሚያዝያ 2003 ዓ.ም. በፊት የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት አመልክተዋልን?

ከሚያዝያ 2003 ዓ.ም በፊት ለጥገኝነት አመልክተው ነገርግን ተቀባይነት ያላገኙ ከሆኑ ሆኖምግን የሆም ኦፊስ ጽህፈት ቤት ውሳኔው በጊዜየው ቢሰጥ ኖሮ የስደተኛነት ፍቃድ ወይም ልዩ የመግብያ ፍቃድ ይሰጥዎት ነበር ብለው የሚያምኑ ከሆነ፡ እባክዎን ቀጥሎ ባለው የረፍውጅ ካውስል (Refugee Council) ድረገፅ ላይ ማብራርያ ያንብቡ። www.refugeecouncil.org.uk/policy/briefings/2007/delays.htm

በዚህ በራሪ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱትን መረጃዎች በተመለከተ ጥያቄ ካልዎት፡ እታች ከተዘረዘሩት የረፍውጅ ኤጀንሲዎችን አንዱ ለማነጋገር ይችላሉ።

**የመጪዎች የምክር መስመር (Migrant Helpline) ዋና ጽሕፈት ቤት (Kent, Sussex)**
ቴሌ: 01304 203 977
www.migranthelpline.org.uk

**የብዙ ባህሎች ምንጭ ማእከል (Multi-Cultural Resource Centre) (Northern Ireland)**
ቴሌ: 02890 238 645
www.mcrc-ni.org

**የሰሜን ኢንግላድ የረፍዩጂ አገልግሎት (North of England Refugee Service) ዋና ጽሕፈት ቤት (North East)**
ቴሌ: 0191 245 7311
www.refugee.org.uk

**ረፍዩጂ አክሽን (Refugee Action) ዋና ጽህፈት ቤት**
**(East Midlands, North West, South Central, South West)**
ቴሌ: 020 7654 7700
www.refugee-action.org.uk

**ረፍዩጂ ካውንስል (Refugee Council) ዋና ጽህፈት ቤት**
**(London, East of England, Yorkshire & Humberside, West Midlands)**
ቴሌ: 020 7346 6700
www.refugeecouncil.org.uk
http://languages.refugeecouncil.org.uk

**ረፍዩጂ ካውንስል በስኮትላንድ (Scottish Refugee Council) ዋና ጽህፈት ቤት (Scotland)**
ቴሌ: 0141 248 9799
Freephone: 0800 085 6087
www.scottishrefugeecouncil.org.uk

**ረፍዩጂ ካውንስል በዌልስ (Welsh Refugee Council) ዋና ጽህፈት ቤት (Wales)**
ቴሌ: 029 2048 9800
www.welshrefugeecouncil.org



Asylum Support Partnership consists of:

Migrant Helpline, charity number: 1088631 www.migranthelpline.org
Refugee Action, charity number: 283660 www.refugee-action.org.uk
Refugee Council, charity number: 1014 576 www.refugeecouncil.org.uk
Scottish Refugee Council, charity number: SC008639 www.scottishrefugeecouncil.org.uk
Welsh Refugee Council, charity number: 1044885 www.welshrefugeecouncil.org.uk